ቁርኣንን ድምፁን ከፍ አድርጎ የሚያነብ ምፅዋትን በይፋ እንደሚመፀውት አምሳያ ነው፤ ቁርኣንን በዝግታ የሚያነብ ምፅዋትን በድብቅ እንደሚመፀውት አምሳያ ነው።

ዑቅባ ቢን ዓሚር አልጁሀኒይ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ: የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም
በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፦ "ቁርኣንን ድምፁን ከፍ አድርጎ የሚያነብ ምፅዋትን በይፋ እንደሚመፀውት አምሳያ ነው፤ ቁርኣንን በዝግታ የሚያነብ ምፅዋትን በድብቅ እንደሚመፀውት አምሳያ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና ነሳኢ ዘግበውታል።]

ቁርኣንን በይፋ የሚያነብ ምፅዋት በይፋ እንደሚሰጥ አምሳያ መሆኑን፤ ቁርኣንን በድብቅ የሚያነብ ምፅዋት በድብቅ እንደሚሰጥ አምሳያ መሆኑን ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ገለፁ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/65055